# *ለዘመናት ታፍነው ለኖሩ የሕዝቡ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ በመስጠት በየአካባቢው እየተከሰቱ ያሉትን ሕዝባዊ ተቃውሞዎች መንግሥት ማስቆም ይኖርበታል!*

### *ከኢትዮጵያ ሶሻል-ዴሞክራቲክ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ*

ኢሕአዴግ የመንግሥት ሥልጣን ይዞ የይምሰል ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ካወጀበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ፣ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ሕዝባዊ ተቃውሞዎች በመንግሥት የተሳሳቱ ፖሊስዎች ላይ እና ሕዝቡም የተለያዩ የይገባኛል ጥያቄዎችን በማንሳት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። እነዚህ የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ በመሆን፣ በተለይ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከሀገር አልፈው የዓለም-አቀፍ ትኩረት እስከመሳብ ደርሷል። ሕዝባዊ ተቃውሞውን ለማፈን በመግሥት በሚወሰዱ እርምጃዎችና በአለመረጋጋቱ አመካኝተዉ ለግል ጥቅም በሚንቀሳቀሱ አፍራሽ ሀይሎች ብዙ የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ በሺዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ በብዙ ሚሊዮኖች የሚገመት የሕዝብና የግል ንብረት ወድሟል፣ ሕዝብ በሚሊዮኖች ተፈናቅሏል።

ለዚህ ሁሉ ጥፋት ምክንያቱ የተሳሳተ የኢሕአዴግ ፖሊሲ ያስከተለዉ የመልካም አስተዳደር መጥፋትና የፍትህና የሀገር ደህንነት ጥበቃ ሥርዓቶቹ የገዢውን ፓርቲ የፖለቲካ ዓላማ አስፈጻሚ ሆነው መቆየታቸው ነው። አስተዳደሩ ከታች ከቀበሌ አንስቶ እስከ ክልልና ፌዴራል መስተዳድር ድረስ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ሳይሆን በኢሕአዴግ ካድሬዎችና ባለሟል ቅጥረኞች በመሞላቱ፣ ሕዝቡን በማዋከብ ሰላሙንና መብቱን አሳጥቶ ሸብር አስፍኖ ቆይቷል። የአርሶ አደሩንና የከተማውን መሬት በመንጠቅ ጥቅም በማጋበስ ለሀገርና የውጭ ከበርቴዎች አሳልፎ ሰጥቷል። በመንግሥት ሥራ የመቀጠር ቅድሚያ በኢሕአዴግ አባልነት ሆኖ፣ የግል ሥራ ዘርፉም በኢሕአዴግ ባለስልጣናት ቁጥጥር ሥር በመሆን በሙሰኝነት የተጨማለቀ ሆኗል። ይህ መጠነ-ሰፊ በደል የኢትዮጵያን ሕዝቦች በመንግሥት ላይ ለተቃውሞ እንቅስቃሴ አነሳስቶታል። በዚህ ረገድ በብዙ የሀገራችን ክፍሎች መረጋጋት ጠፍቶ ሕዝቦች በኢሕአዴግ ታጣቂ ካድሬዎች መሪነት ወገን እየለዩ የሚጋጩበት ሁኔታ ለመፈጠሩ ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

1. የአስተዳደር ክልሎች አከላለል ጥያቄዎች መመለስ የነበረባቸው በሕገ-መንግሥቱ መሠረት መሆን ሲገባው፣ ሥርዓት አልበኛ የኢሕአዴግ ካድሬዎች የልዩ ጥቅም ማካበቻ አድርገውት ከመቆየታቸውም በላይ፣ የኢሕአዴግ የበላይ መሪዎች አምባገነን ውሣኔዎች ውጤት ሆኖ መቆየቱ የማያባሩ ተቃውሞችን ሲያስነሣ ቆይቷል። ለአብነት ያህል በሽግግሩ ወቅት አዋጅ 7/1984 መሠረት በአካባቢው ሕዝቦች ተወካዮች ስምምነት ከክልል 7 እስከ 11 የተዋቀሩት ክልሎች፣ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሕገ ወጥ ትዕዛዝ በአንድ ላይ ተጨፍልቀው «የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል» እንዲባሉ በአምባገነንነት መወሰኑ በዚያ የሀገራችን አካባቢ ለሚነሱ የአከላለል ጥያቄዎች መነሻ ነው። በመሆኑም ክልል 8 ሆኖ ተከልሎ የነበረው አካባቢ ሕዝብ ለረዥም ዓመታት «የሲዳማ ክልል» ዕውቅና ካልተሰጠው በማለት ትግል እያካሄደና ክቡር መስዋዕትነት እየከፈለ ይገኛል። እንደዚሁም ክልል 11 የነበረው አካባቢ «የደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል» ጥያቄ የሚባል እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቷል። ስለዚህ በደብብሕ ክልል ውስጥ የተረጋጋ ሁኔታን ለመፍጠር፣ የቀድሞውን አምስቱን ክልሎች መልሶ ለማዋቀር የሚያስችል አስቸኳይ መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል።

2. የነዋሪውን ሕዝብ ይሁንታ በዴሞክራሲያዊ አግባብ ያላገኙና በካድሬዎች ትዕዛዝ የሚፈፀሙ አከላለሎች የማያባሩ ተቃውሞዎችንና ግጭቶችን እያስነሱ ስለመሆኑ የወልቃይት-ጠገዴ፣ የራያ፣ የሸካ፣ የቅማንት፣ የአርጎባ፣ የኮንሶ፣ የጎፋ፣ ወዘተ አካባቢዎች ጥሩ ማሳያዎች ናቸው። ከዚህም የተነሣ፦
   - ኦሮሞ ከሶማለና ከቤኒሻጉል-ጉሙዝ፣
   - የጉጂ ኦሮሞ ከቡርጂና ኮሬ፣
   - አማራ ከትግራይና አርጎባ፣
   - አፋር ከኢሳ-ሱማሌ፣
   - ጉራጌ ከሀዲያ፣ ቀቤና እና ማረቆ፣
   - ኦሮሞ ከየም ጋር

   እና ሌሎችም ዘወትር የሚጋጩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ችግሬ በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሰረት በሕዝበ-ውሣኔ እልባት እንዲያገኝ አስቸኳይ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል።
3. «ብሔራዊ የአስተዳደር እርከን ይሰጠን» በማለት የሚነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ያልተሰጣቸው ስለሆኑ ከፍተኛ ተቃውሞዎችን እያስነሱ ቀጥለዋል። በአሁኑ ወቅት የጎፋ ሕዝብ የዞን ጥያቄ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ቀስቅሶ የሳውላ ከተማን ለመጠነ-ሰፊ የንብረት ውድመት ዳርጓል፣ ዜጎችም ለአካል ጉዳትና እሥራት ተዳርገዋል። በሸካ ሕዝብ ላይም እየደረሰ ያለው የሕይወት መጥፋት፣ እሥራትና ስደት እጅግ ዘግናኝ ነው። እንዲሁም በኮንሶ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ደረጃ የደረሰ ጭፍጨፋ ተካሄዷል።
4. «ብሔር/ብሔረሰባዊ ማንነታችን ይታወቅልን» የሚል ጥያቄ አንስተው በመታገል ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ ላሉ ሕዝቦች ፍትሃዊ ውሳኔ ያለመሰጠቱ በሀገራችን ለሰላምና መረጋጋት መጥፋት አንዱ ምክንያት ነው። በዚህ ረገድ በምሳሌነት፦ የወለኔ፣ የዳንጣ ዱበሞ፣ የአርሲ ሀዲያ፣ የወላይታ ሀዲያ እና በሶማሌ ክልል የኤረር ባሬ ሕዝቦች ጉዳይ ለአብነት የሚጠቀስ ነው። ይህ የማንነት ጥያቄም በጥናትና በሕዝበ-ውሣኔዎች ላይ በመመስረት አስቸኳይ መፍትሔ ሊያገኝ ይገባል።
5. ከ«ብሔራዊ ክልላቸው» ውጪ የሚኖሩ በቁጥራቸው አናሳ ሕዝቦች የዜግነት መብት ያለመከበር ጉዳይ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት እየተፈታተነ ያለ ትልቅ አደጋ ሆኖ እያለ፣ ሕጋዊ እርምጃዎችን ወስዶ ሥርዓት ሳያስይዝ የኢሕአዴግ መንግሥት በቸልታ እያለፈው ቆይቷል። ይህም ዜጎች በመረጡት ክልል ተዘዋውረው መኖር፣ ኑሮአቸውን መመስረትና ሀብት/ንብረት ማፍራት እንደሚችሉ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገውን የጣሰ እንደመሆኑ፣ የዜጎችን የኢትዮጵያዊነት መብት ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎታል። በዚህ ረገድ፦
   - ከሚሊዮን የሚበልጡ የኦሮሞ ተወላጆች ከሶማሌ ክልል፣
   - በመቶሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ሶማሌዎች ከኦሮሞ ክልል፣
   - በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አማሮች ከኦሮሞ፣ ከደቡብና ከቤንሻንጉል ክልሎች፣
   - የትግራይ ተወላጆች ከአማራና ከሌሎችም ክልሎች፣
   - የጌድኦ ሕዝብ ከኦሮሞ ክልል፣
   - የወላይታ ሕዝብ ከሲዳማ (በተለይም ከሀዋሳ ከተማ)፣
   - በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሲዳማዎች ከኦሮሞ ክልል፣

«ከክልላችን ውጡ» በሚል የኢሕአዴግ ካድሬዎች ስውርና ግልፅ ቅስቀሳ፣ ንፁህ ዜጎች ላይ ከንብረት ውድመት አንስቶ ሕይወት መጥፋትና ስደት ድረስ እየተፈፀመባቸው

መሆኑ በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተት ነው። ስለሆነም አዲሱ የኢሕአዴግ አመራር ከማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ በመስጠት፣ ከሁሉም ክልሎች የተፈናቀሉትን ዜጎች ወደነበሩበት ቀዬአቸው መልሶ በማቋቋም ኃላፊነቱን እንዲወጣ አበክረን እንጠይቃለን።

እንደዚሁም ብልሹ አስተዳደርና ሙሰኝነት ያንገሸገሸው ሕዝብ በኢሕአዴግ ስርዓት ላይ ያለውን ተቃውሞ ለመግለጽ ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች መነሻነት ከፍተኛ ጉዳት በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እየደረሱ መሆናቸው እየሰፋ መሄዱ እጅግ አሳቢ ሆኗል። ከነዚህም መካከል በዎላይታ ሶዶ እና በቅርቡም በጻውሮ ዞን የተከሰቱት ሕዝባዊ አመጾች ያደረሷቸው ጉዳቶች ከፍተኛ ናቸው። ይህ የሚያሳየው ሀገራችንን አረጋግቶ ሰላማዊ ሁኔታ ለመፍጠር የመልካም አስተዳደር ጥያቄ አስቸኳይ መፍትሄ እንደሚያሻው ነው።

አዲሱ ጠ/ሚር እየሰጡ ከሚገኙት የተስፋ ቃል፣ ከወሰዱአቸው ገንቢ እርምጃዎች እና የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ቀርበው በማነጋገር የወሰዱት የማቀራረብ እርምጃ በአጠቃላይ በበጎ ጅምርነት የምንመለከታቸው እርምጃዎች ቢሆኑም፣ እስከ ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ መረጋጋት እንዳይኖር፣ በተለይም የተወሰኑ ብሔር ተወላጆችን የጥቃት ኢላማ በማድረግ ለሚፈጠሩ ግጭቶች፣ ጠባብ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚፈልጉ ኃይሎች በየቦታው ሥራ-አጥ ወጣቶችን በማደረጀት ሲያንቀሳቅሷቸው እየታየ ፣ ይህንን አፍራሽ እንቅስቃሴ በሚያደርጉት ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሲወሰድ አይታይም። በዚህ ረገድ፦

- ሰሞኑን በሻሼመኔ ከተማ የተከሰተው ረብሻና የጭካኔ ግዲያ፣
- በቅርቡ በጅጅጋና ሌሎች የሶማሌ ክልል ከተሞች የሶማሌ ብሔር ባልሆኑ ነዋሪዎች ሕይወት፣ ንብረት እና ቤተ ክርስቲያኖቻቸው ላይ የደረሰው ጥቃት፣
- በሀዋሳ ከተማና አካባቢው በወላይታ ብሔር ተወላጆች ሕይወትና ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት፣
- በወልቂጤ ከተማ ላይ በቀቤና ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረው ጥቃት፣
- በጣና በለስ በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰው አደጋ፣
- በደበረ-ማርቆስ ከተማ በግለሰቦች ላይ ያነጣጠረው ጥቃት እና ሌሎችም በከፍተኛ ደረጃ ለሀገሪቱ መረጋጋት የስጋት ምንጭ ናቸው።

ስለዚህ «ሳይቃጠል በቅጠል» እንዲሉ መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ እየተዛመተ ባለው የአፍራሽ ኃይሎች እንቅስቃሰዎች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶና ተከታትሎ ሥርዓተ-አልበኝነትን ማስቆም ከምንም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን በአንክሮ ማስገንዘብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሶሻል-ዴሞክራቲክ ፓርቲ /ኢሶዴፓ/
ነሐሴ 9 ቀን 2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ